# <u>ሚሽን ደብተራው</u>
# <u>ሰዩ አብርሃን በራሱ መድረክ ላይ ልቡን</u>
# <u>በፈንጂ ሰብሮ አሞቱን በማፍሰስ አጋልጦ</u>
# <u>ቀሚስ አልብሶታል</u>

ከአስተዋይ በቀለ

**ቪቫ ጀግናው ወጣት ታዘበው አሰፋ ! ሳንጃህ ሰው በላ !**

ሰዬ አብርሃ ከወያኔ ብሎም ከኢህአዴግ ጋር እትብቱን ያልቆረጠና ቁርባኑን ያላፈረሰ የፖለቲካ ወስላታና የተቃዋሚዎችን ሜዳ በቡልዶዘር አፍርሶ ለመደልደል ጥፋት የተላከ ሰላይና አሻጥረኛ ነው ።

ይህ ወስላታ ወንጀለኛ ሰው የኢትዮጵያን ነባር የአገር መከላከያ ተቋሞችን ያፈረሰ፣ ኤርትራን ያስገነጠለና ሌላም ብሔራዊ ደባዎችን በጥብቅ ምስጢር የፈጸመ ከመለስ ተለይቶ የማይታይ መልቲ ፀረ_ ኢትዮጵያ ፀረ_ሕዝብ ነው ።

በወያኔ እርኩስ አባልነቱና ከመለስ ጋር በነበረው የትምህርት ቤት ጓደኝነት ***የመከላከያውን ትልቅ ቦታ ይዞ ቢጋርዮሽ አመራር አብሮ ብዙ የወሰነና ብዙ ያጠፋ ከመሆኑ ጋር በተለይም የአውደ ውጊያና የፖለቲካ Incommunicado Prensa በሆኑ ታጋዮች ጉዳይ ቀዳሚና ዝርዝር የሆነውን Visa a Fronte ሚና በመጫዎት <u>ያሳፈነና ዳብዛቸውን የሰወረ</u> በመሆኑ ምንጊዜም በዋናነት ተጠያቂ ነው ።***

ታዘበው አሰፋ እንዳለው ስለ ፍትህ መናገርና እውነተኛ የወያኔ ተቃዋሚነቱን እንድናምንለት ከፈለገ የፖለቲካ እስረኞችን ጉዳይና ሌሎችንም በአገርና በሕዝብ ላይ የተፈጸሙትን ወንጀሎች ሁሉ ሳይሸሽግ በአደባባይና በመገናኛ ብዙሃን ማጋለጥ፣ ሕዝባችንን ይቅርታ መጠየቅና በወንጀሉ ለመከሰስ ፈቃደኛ ሆኖ መቅረብ አለበት ።

ታለበለዚያ ግን፣ በለበጣ እንደ ጲላጦስ ከደሙ ንፁህ ነኝ፣ አላውቅም ወይም የኢትዮጵያ ሕዝብ ተሰብስቦ ይጠይቀኝ እያለ በማላገጥ የአውደ ውጊያና የፓለቲካ እስረኞችንና ሌላውንም የወያኔ ወንጀሎችና ጉዶች ሁሉ እየደበቀን መኖር ስለማይችል የተቃዋሚውን ክልል በአስቸኳይ ለቅቆ ወደ መጣበት ወደ ወያኔ አፎቱ ተመልሶ ቢገባ ይሻለዋል ።

ጀግናው ወጣት ታዘበው አሰፋ በመድረክ መድረክ ላይ ያቀረበው ጥያቄና የሰጠው አስተያየት ሕጋዊና አንገብጋቢ ብሔራዊ የፖለቲካ ጥያቄና ትኩረት ነው ። **ለዚህ መልስ እስካልተገኘ ድረስ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጨርሶ አይተኛም።**

የታዘበው አሰፋ ድርጊት መላ የኢትዮጵያን ሕዝብ ያኮራና ያስደሰተ ከመሆኑ ጋር የኢትዮጵያን ወጣት ሁሉ ያነቃቃና ለሚጠበቀው ትግልና ኢንቲፋዳ አርአያና ምሳሌ የሆነው ትልቅ ቀስቃሽ ጀግንነት ነው ።

ጀግናው ታዘበው አሰፋ የማይታጠፍ ወኔ፣ የጋለ ቁጭት ያለው አገሩን የሚወድ ቆራጥ ታጋይ ከመሆኑ ጋር፣ የፖለቲካ ብስለት ብሎም የአመራር ብቃት እንዳለው ለኢሳት ከሰጠው ቃለ ምልልስ ለመረዳት ተችሏል።

በዚህ ትክክለኛና ሕጋዊ የፖለቲካ ጥያቄ ባቀረበ ጀግና ወጣት ታዘበው አሰፋ ላይ አንድ ጠንቅ ቢፈጠር በኢትዮጵያ፣ በሕዝቧና በሰንደቅ ዓላማዋ ላይ እንደተፈጸመ ተቆጥሮ ተጠያቂው መድረክና መሪዎቹ በተለይም ሰዪ አብርሃ እንደሚሆን በግልጽ ካሁኑ መታወቅ አለበት ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ያሸንፋል ! !

ወንጀለኞች ተጋልጠው በሕግ ይጠየቃሉ !